የዘር ፓለቲካና በህፃናት ላይ ሊያስከትል የሚችለው የስዕነ አእምሮ ችግር

:::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::

ከጌትነት ሠለሞን

ዕለት 08/09/2020

ይህን ፅሁፍ እንድፅፍ ያነሳሳኝ ምክንያት የዛሬ ሁለት ወር አካባቢ የአርቲስት አጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ስበብ በማድረግ ኦሮሚያ ክልል ተብሎ በሚጠራው የኢትዩጰያ ግዛት ውስጥ ነገድን/ethinicty እና ሀይማኖት ላይ ያነጣጠረ የዘር ማጥፍት ተግባር መደረጉን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መመልከት በመቻሌ ነው:: ለዚህ የዘር ጭፍጨፍ ምክንያት የሆነው ደግሞ አገሪቱ እየተከተለችው ያለው ዘርን ያማከለ ህገ መንግስት እና አወቃቀር ነው:: ይህ በአገሪቱ ለ30 ዓመት ተንሰራፍቶ ያለው የዘር ፓለቲካ የቀደመችውን ኢትዩጰያ በማፍረስ በምትኩ ቁዋንቁዋን መስረት ያደረገ የልዩነት አጥር በማጠር አሁን ላለንበት ውጥንቅጥ እና ሰርዓት አልበኝነት ዳርጎናል:: የዚህ የዘር ፓለቲካውን ደግሞ የባስ  መራር ያደረገው አሁን ያለችውን ኢትዩጰያ ለመመስረት ያልነበረን ትርክት እንደነበረ በማድረግ ትውልዱን በዚህ እኩይ በሆነ ትርክት ኮትኩቶ በማሳደግ ለመጥፎ ነገር መጠቀሚያ በማድረግ ነው::

የትምህርት ካሪከለሙ ጥላቻን በማስተማር አሁን ቄሮ ተብሎ የሚጠራውን የህብረተሰብ ክፍል አውሬ ሆኖ እንዲያድግ ምክንያት ሆኖል::የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዘዳንት የሆኑት አቦ ሺመልስ አብዲሳ እንደነገሩን: እጠቅሳለሁ" ቄሮን የመሰረትነው እኛ ነን ቄሮን መንገድ ዝጋ ስንለው ይዘጋል ክፈት ስንለው ይከፍታል" ብለው እንዴት ክቡር የሆነውን የሰው ልጇ ለሚፈልጉት እኩይ አላማ መጠቀሚያ እንዲሆን በማስብ ምንም ዓይነት የሞራልም ሆነ ፈራሂ እግዚህዓቤር እንዳይኖረው አድርገው እንዳሳደጉት ከዛሬ ሁለት ወር ገደማ በኦሮሚያ ክልል የሆነውንና በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ስጋት በማየት ማረግጋገጥ ይቻላል:: በእውነቱ ይህ የሰውን ልጇ ወይንም ቄሮን ለተወሰኑ የፓለቲካ ድርጇት መሪዎች የፓለቲካ ስልጣን መቆያ እንዲጠቅም ተደርጎ ስብስቡ/ቄሮን በዘዴ ከእራሱ እውቅና ውጭ manupulate በማድረግ ለእኩይ ተግባር ማዘጋጀት አቦ ሺመልስንም ሆነ ድርጇታቸውን ብልፅግናን በስብዓዊ መብት ጥሰት እንዲጠየቁ የሚያስችል አለም አቀፍ የህግ ድንጋጋጌ ሰለሚኖር በዚሁ ዘርፍ እውቀቱ ያላችሁ የህግ ባለሞያ ኢትዩጰያውያን እንድታስቡበት እላለሁ::

የእኔን ትኩረት የሳበው ብዙዎች ያላዩት የመሰለኝን እና ይህን አረመኔያዊ የዘር ማጥፍት ድርጊት በአይነ ሰጋቸው በተመለከቱ የነገ አገር ተረካቢ ህፃናት ላይ የሚያሳድረው የሰነ ልቦናም (psychological) ሆነ የስነ አእምሮ (Neuropsychological) ችግር ለማመላከትና በስነልቦና ህክምና ዘርፍ ተሰማርተው ላሉ ወገኖች እነዚህን ህፃናት እርዳታ በመስጠት እንዲታደጎቸው ለማሳሰብም ነው::

በመጀመሪያ ደረጃ እነ አቦ ሺመልስ ያሳድጎቸውን ቄሮዎች ከሰውነት እንዴት ወደ አውሬነት እንደቀየሩቸውና እነዚህ ወደ አውሬነት የተቀየሩት ቄሮዎች ደግሞ ምንም በማያውቁ ሌሎች ህፃናት እና ወላጆቻቸው ላይ የፈፀሙት አረመኔያዊ ተግባር በክልሉ በሚኖሩ ህፃናት ላይ የሚያስከትለውን የስነ ልቦና ችግር ለማሳየት እሞክራለሁ::

አንድ ግለስብ ሁሌ በራሱ ዛቫያ እራሱን ማእከል አድርጉ ሲዞርና ለሌሎች ደህንነት ደንታ ቢስ ከሆነ የስነ ልቦና ሀኪሞች egocentric or Narcissstic/ግለኛ ዎይንም እራስ ወዳድ ይሉታል:: ታዲያ ይህ ችግር በወቅቱ ተገቢውን ህክምና ካላገኘ ውሎ አድሮ የስብዕና ችግር/personality disorder[1] የተባለ የስብዕና ችግር ያሳድግና በአዎቂነት ዘመኑ ከብዙ ነገሮች የተገለለና ውሎ አድሮም በእራሱ ላይ ጉዳት ሊፈጥር ይችላል:: ምንያቱም ለሎች ስዎች ደንታ ሰለማይኖረው ስዎች እንዲሸሹት ይሆናል:: ልክ እንደ egocetric/ግለኝነት ችግር ethinocenrisme[2]/ ነገዳዊነትም/ዘረኝነትም በራሱ ነገድ ዙሪያ የሚሽከረከር ይሆንና ከእሱ ውጭ ላሉ ነገዶች ጥሩ አይነት እይታ አይኖረውም:: አግላይ ይሆናል:: እንደ አንድ ያገር ሰው እንደ ሊም ያያዙን

---

[1] https://psykolog-erne.dk/at-vaere-egocentrisk/?cn-reloaded=1

[2] Marianne Skytte familier og socialt arbejde (2007) P.21

ነገሮችን ወደ ዳር በግፋት » እናንተ እና እኛ»የሚል (Dicotomy) በምፍጠር የነበረውን ማህበራዊ እሴት በማዳከም የእኔ ነው ለሚለው ጎሳ በማድላት ባህል ዝግ እንደሆነ በመመልከትና ማህበራዊ ትሰሰሩም የእኔ ከሚለው ዘውግ ብቻ እንደሆነ በማሰብ ባህል ከተለያዩ ሰዎች ጋር በሚደረገግ እለታዊ መስተጋበር እደሚቀየርና እንደሚያድግ የካደ essentaliatistic aspect[3] እንዳለው ያሳየናል። ይህ ማለት ደግሞ ሰዎች ባህልን በሚያደርጉቸው ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዳያያሳድጉ ሰለሚያደርጋቸው ባህል በተወሰነ ጎሳ ብቻ ታጥሮ እንዲቀርና ዲያለክቲካዊ መስተጋበሩን በሰራዓቱ እንዳያከናውን ይገደበዋል። ይህ አመለካከት ታዲያ ወደ መቀራረበና ወደ መፍትሄ ሳይሆን ወደ ዘር ፍጂት እየዎሰደን ለመሆኑ የቄሮን ተገባር በኦሮሚያ መመልከት ከበቂ በላይ ማስረጃ መሆኑን እናያለን። ይህም ደርጊት የማህበራዊ እብደት እንዳስከተለብን እንኻን እኛ አለመም እያየው ያለ ሃቅ ነው።

<u>የእነ አቦ ሺመልስ አብዲሳ ቄሮን ለሚፈልጉት የፓለቲካ አላማ ማስፈፀሚያ እንዴት እንድተጠቀሙበት social psychology/ የማህበራዊ የስነ ልቦና ቲየሪን በጉዳዩ ዙሪያ የሚለውን እንመልከት::</u>

እንደ ማህበራዊ የስነ ልቦና ቲየሪ (Socialpsychology) መሰረት የሰው ልጂ ሲፈጠር "በጎ" ወይንም "መልካም" እንደሆነ አስተምሁሮቱ ቢናገርም እንደ ሲግሞን ፍሮይድ ያሉ የስነ ልቦና ሀኪሞች ደግሞ ሰው ሲወለድ ልክ እንደማንኛውም እንስሳት "agression & sexual drive[4]" በውስጡ ይዞ ሰለሚወለድ በፍላጎቱና ጥቅሜ ነው በሚለው ነገር ከመጡበት የጭካኔ ሰይፋን ከመመምዝ ወደ ሁላ እንደማይል ሲግሞን ፍሮይድ ይናገራል:: ምክንያቱም የሰው ልጂ በፍላጎቱ ሰለሚመራ:: ሰው ፍላጎቱን ሲገራ ከፍላጎቱ ይልቅ በአመክንዮ ሲመራ አውሬ መሆኑ ቀርቶ ሰው ይሆናል:: በኦሮሚያ ክልል እየሆነ ያለውም ይህ ነው። በክልልህ አማራ የሚባል ሰፋሪ መጥቶ በአገርህ ሃብት አፍርቶ በሰላም እየኖረ አንተ በገዛ አገርህ የበይ ተመልካች ትሆናለህ በሚል ትርክት በወጣቱ ላይ ቁጭትን በፍጠር በሃይል በሺብር እና በግድያ በመታገዝ ጥቅሜን ፍላጎቴን አስከበራልሁ በሚል በጣም ሁላ ቀር በሆነ አስተሳሰብ እየተመራ አገራችንን እንደገና ወደ ጫካው ህግ እየመለሱዋት ይገኛሉ።

ሲግሞን ፍሮይድ psycho analysis በሚለው ቲየሪ የሰውን ልጂ ስብዕና/personality structure በሶስት ይከፍለዋል በአማርኛ ለመተርጉም ሰለቸገረኝ የእንግሊዝኛውን ቃል እጣቃማለሁ::እነሱም: ID, Ego and superego ብሎ ይከፍላቸዋል:: የID ተቀዳሚ ስራ ህመምና ቸነፈርን ማሰወገድ ሲሆን ቅድም ከላይ እንደጠቃስኩት agression drive and sexual need በዉስጡ በመያዝ የሰውን ልጂ የፍላጎቱ መርኮኛ በማደርግ ego ለሚባለው የስብዕና ክፍል ግብዓት በመሆን superego/moral/ፈራሂ እግዚሃር እንዳይኖር በማድረግ ከህግና ሞራል በማፈንገጥ በፈላጎቱ በመመራት ጥቅሙን ለማስከበር ማንኛውንን ግፍ ከመፈፅም ወደ ሁላ እንደማይል እናያለን:: ይህ የሚሆነው ግን ከልጂነት ዘመን ጀምሮ ፈላጎቱና ቁጣውን የሚያስተናግድበት መንገድ ካለተፈጠረለት ነው። የሰው ልጂ ባህሪ ከጂመሩ ካልታረቀና በሰራዓት ካልተያዘ ሲያድግ ችግሩን እናሰተካከላለን ማለት ከባድ ነው የሚሆነው።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የሲግሞን ፍሮይድ ቲየሪ ከዛሬ 100 ዓመት ገደማ የሰውን ልጂ ጨካኔያዊ ባህሪ ለመግለፅ ሞያተኞቹ ሲጠቀሙበትና አሁንም በሰራ ላይ ያለ ቲየሪ ነው:: ከ1970 በሁላ የመጣው የማህበራዊ የስነልቦና አስተምህሮ ደግሞ የሰው ልጂ ከዉለደቱ ሰላማዊና መልካም እንደሆነ ይገልጽና ሰዎች ጭካኔን የሚላመዱት ከዉለደት በሁላ በአሰተዳደግ እና በአካካቢ ተጽዕኖ ምክያት እንደሆነ የዘርፉ ባለሞያዎች የናገራሉ። የሰዋችን የጭካኔ ጥግ ምንጭ structural violence[5] ውጤት እንደሆነም የማህበራዊ ሳየንስ ባለሞያዎችም ይናገራሉ:: መንግስት መዋቅሩን አደራጂቶ ወጣቶችን ከልጂነት ጀምሮ ጥላቻን እየመገበ ክቡሩን ሰው ከሰውነት ወደ "ቄሮነት መንጋ" በመቀየር በአገሪቱ ውስጥ ህግና ስርዓት እንዳይከበር ምክንያት ሆኖል የመንለውም ለዚህ ነው::

---

[3] Ibid.

[4] Gunn Strand Hutchinson & Siv Oltedal (2006) P.44

[5] http://www.structuralviolence.org/structural-violence/

ስው ፍላጎቱን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ regulate ማድረግ ካልቻለ እንስሳዊ ባህሪው ያጋድልና ለህብረተስብ አደጋ ይሆናል ማለት ነው:: ይህን የስው ልጇ ባህሪን ደግሞ regulate ማድረግ የሚገባቸው የሀይማኖት ተቋማትና መንግስት ተብየው ነበሩ:: ሀይማኖትን የወያኔ መራሹ እና አሁን የቀጠለው መንግስት ጥቅም እንዳይኖራቸው አድርገው በማዳከማቸው ምክንያት ተስሚነታቸው እንዲቀንስ ሆኖል:: መንግስት የተባለውም ተቋም ደግሞ አገሪቱን በዘር ከፋፈሎ አብሮነትን በማጥፋት ልክ እንደ ጫካው ህግ ጉልበት ያላው "መንጋ" ከህግ በላይ ሆኖ ዜጎችን በጭካኔ እንዲጨርስ ሁኔታውን በማመቻቸት ያለ ለመሆኑ "ቄሮ" ያረጋግጥልናል::

የሰነልቦናው ሀኪም ሲግሞን ፍሮይድም ሆነ የማህበራዊ የሰነልቦና ቲየሪ አቀንቃኞች ለእኔ ሁለቱም ትክክል ናቸው:: የሰነልቦና ሃኪም በግለሰብ ችግር ዙሪያ የሚሰራ ሲሆን የማህበራዊ የሰነልቦና ሃኪም ደግሞ የህብረተሰብን የሰነልቦና ጉዳይ የሚያይ ባለሞያ ነው። የግለሰብም ሆነ የህበረተሰብ የሰነልቦና ሃኪሞች የሰውን የውስጥ ማንነት ”ጭካኝ” እና ”ደግ” የሆነ ማንንነት የያዘ መሆኑን የገለፁበት መንገድ በትክክል የሰውን ልጇ የውስጥን ተቃርኖ በትክክል ያሳየ ነው። ምክንያቱም ምንም እንኳን የሰው ልጇ እግዚህዓቤር በአምሳሉ የፈጠረው ፍጡር ቢሆንም የስውን ልጇ አእምሮ አካባቢና ተፈጥሮ ጫና ሰልሚያደርጉበት ሰው የአካባቢም የተፈጥሮም ቅይጥ ውጤት መሆኑን ያሳየናል:: ስውን በእንክብካቤና በፍቅር ካሳደከው "ሰው" ይሆናል ስውን በጥላቻና ፍቅር ነስተህ ካሳድከው ደግሞ "እውሬ" ሊሆን እንደሚችል በአገራችን እያየን ያለውንና የቄሮን ባህሪን ማየት በቂ ማስረጃ ነው:: ለዚህ ነው ብልፅግናንም ሆነ የተቀሩትን የኦሮሞ ፅንፈኞች በህግ ይጠየቁ የምለው:: ምክንያቱም ክቡሩን የሰው ልጇ ከልጇነትጀምረው ጥላቻን በማሰተማር አውሬ እንዲሆን  ሰለአደረጉት::

የኦሮሞ ፅንፈኞች እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የስው ልጆች ”ቄሮን” ለራሳቸው ስልጣን ማራዘሚያ በማስብ እንዴት ክፍ እና ጨካኝ አድርገው በማሳደግ በራስቸው ወገኖች በሆኑ ኢትዩጳያውያን ላይ ጭካኔ በተሞላበት መልኩ በሀይማኖታቸውና አማራ እና ጉራጌም ሰለሆኑ ብቻ የዘር ማጥፉት ወንጀል እንዴት ሊፈፅም እንደቻሉ አይተናል:: ምክያቱም የኦሮሞ ፅንፈኖች ፈላጎት እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ዎገኖችን ከኦሮሚያ ክልል እንዲወጡ ማድረገና Homogenious oromo society መፍጠር ሰለሚፈልጉ::፣ልክ ፍሮይድ እንዳለው የኦሮሞ ፅንፈኖች ፈላጎታቸውን ለማሙላት ቄሮን ተጠቅመው ሺብር በመንዛት ፈላጎትን ማሙላት እንደሚቻል መፈለግን ያሳያል (aggression drive)::

<u>ይህ አረመኔያዊ ድርጊት በህፃናት ሰነልቦና ላይ ጥሎት የሚያልፈውን ጠባሳን ደግሞ እንይ::</u>

የዛሬ ሁለት ወር ገደማ በኦሮሚያ ክልል የተፈፀመውን የዘር ማጥፍት ወንጀል ህፃናት ተመልክተዋል: ወላጆቻቸው ወይንም ስው ሞቶ በጭካኔ ሲበላለት ሲቃጠል አይኑ ሲወጣ ቁመው ያዩ ሰለነበር በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ውሎ ሲያድር በልጆች ላይ ሊያስከትለው የሚችለው የሰነ ልቦና ችግር ከባድ ይሆናል:: ሰለዚህ በዚህ የዘር ማጥፍት ሰለባ ለሆኑ ህፃናት ትኩረት ሰጥተን ልጆቹን ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የስነልቦና ችግር ካልታደግናቸው ህፃናቱ ለከፋ ችግር ይጋለጣሉ:: ሰለዚህ በዚህ ዘርፍ ዙሪያ ያላችሁ ኢትዩጳያውያን ህፃናቱን እንድትታደጉ በአፅኦት አሳስባችሁ አለሁ::

ልክ እንደ ሲግሞን ፍሮይድ የሰእነ አዕምሮ (Neuropsychology) ሳይንቲስቱ Martin H. Teicher and Jacqueline A. Simonsonም (Annaul Reserch Review 2017) በሚለው ፁሁፋቸው የስውን ልጇ እንጉል በሦስት ከፍለው ያዩታል::  ልጆች ገና በእንጭጭ እድሜቸው ሊደርሰባቸው ወይንም ሊያዩት የማየገባ ነገር ካዩ PTSD በተባለ የአእምሮ ጥብሰት/disorder ተጠቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ፡ይናገራሉ። PTSD ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከታች ፡ባጭሩ ለመግለፅ እሞክራለሁ: ከዛ በፊት ግን አንጎል የተባለውን የሰውነታችንን ክፍል በሦስት ከፍለን እናየውና ሰወች አስቸጋሪ በሚባል የሂዎት ጫና ወስጥ ሲያልፉና PTSD በተባለው የአእምሮ ችግር ተጠቂ ሲሆኑ የትኛው የአንጎላችው ክፍል ጋር ነው ግንኙነታቸው የሚለውን ከዚህ በታች እናያለን።
1ኛ Riptails Brian 2ኛ. Limbisk/emotional Brian 3ኛ Frontallappen/Rational/Logical Brian[6] ብለው ይመድቡታል::

[6] Ida Skytte Jakobsen, Mona Ditlevsen & Godette Walmod (2017) p.122-123

1. **Riptials Brian** የሚባለው የአንጉል ክፍል የስው ልጂ ጥንታዊ አንጎል ሲሆን የሚገኘውም በስተሁላችን ከጀርባ አጥንታችን ጋር የሚገናኘው የአንጎላችን ክፍል ሲሆን ታዲያ ይህ የአንጎላችን ክፍል ከተሳቢ እንስሳት ጋር የምንጋራው ጥንታዊ የአንጎል ክፍል እንደሆነ የአዝጋሚ ለውጥም ሆነ የስነ አእምሮ ተመራማሪዎች ይናገራሉ:: የዚህ የአንጎል ክፍል ጥቅም ደግሞ ደመነብሳዊ በሆነ መልኩ ማለትም ከስው ልጂ ቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ አንዳንድ ነገሮችን ያከናውናል:: ለምሳሌ እራሰን ከጠላት ለመከላከል እና በሂዎት ከአደጋ ተጠብቀን እንዴት መኖር እንደመንችል ደመነብሳዊ በሆነ ሂደት እንድናከናውን ይረዳላል: ከሰው ቁጥጥር ውጭ የሆነው ነገር ሁሉ በዚህ የአንጎል ክፈላችን ነው የሚከናዎነው ለምሳሌ የስውነት ሙቀታችንን; እርሀብ ሲሰማን: መተንፈስን እና የወሲብ ፍላጎታችንን የመሳስሉ ደመነብሳዊ ክንዋኔዎች በዚህ ጥንታዊ በሆነው ክፍል ውስጥ ይከናወናሉ ማለት ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ክንዋኔዎች እንሰሳትም ከሰው ጋር ይጋሩቸዋል:: በዚህ የአህምሮ ክፍል "ማስብ" የሚባለው ነገር አይከናወንም:: ሳይንሱ እንደሚለው ሰው ማህበራዊ እንስሳ ነው:: የሰው ልጂ ቆይቶ በአዝጋሚ ለውጥ Limbisk & Frontallappe ወደ ተባለው የስው ልጂ አህምሮ የእድገት ደረጃ ከመድረሱ በፊት በ Riptials Brian ደመነብሳዊ እንቅስቃሴ እየተመራ ከሌሎች እንስሳትጋር እየተጋፍ ከላይ የተጠቀሱትን ፍላጎቶቹን ማለትም እርሀብን: ጥማትን ወሲብንና ሌሎችን ፍላጎቶች ለማሙላት ከቦታ ቦታ ይባዝን ነበር:: እንደ ዛሬው የስው ልጂ ሰልጥኖ በህግና በሞራል ሳይገዛ በጫካ ህግ ውስጥ በነበረበት ግዜ ( ለነገሩ አሁንም በአገራችን ህግና ሞራል ጠፍቶ ቄሮ የተባለው አውሬ ኢትዩጲያንና ኢትዩጲያዊያንን ወደ ጫካው ህግ ወደ ሁላ መልሶናል) ጉልበት ያለው የፈለገውን በሃይሉ የፈለገውን በሚያደርግበት ግዜ (the surviaval is the fittest) :: በዚህ ግዜ አሁን ስው የሆነውና ሌሎች እንሰሳት እራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከል የሚጠቀሙበት የጋራ የሆነውንና ጥንታዊዊውን Raptials Brian በሚባለው የአንጉል ክፍል በመታገዝ ነበር እለታዊ ሂዎታቸውን ይገፉ የነበሩት:: አደጋ በመጣ ግዜ ማለትም አንድ ሌላ ትልቅ እውሬ ድንገት መጥቶ አደጋ ሊሆንባቸው በሚሞክር ግዜ ምንም ሳያስቡ ዘለው የመጣውን አውሬ ይገጥማሉ: ወይ አውሬው ትልቅ ይሆንና አደጋ ይጥልብናል ብለው ካሰቡ ደግሞ እሩጠው ያመልጣሉ አለበለዚያ ደግሞ በአሉበት በድንጋጤ ፈዘው እንዲቀሩ ይሆናል:: ይህ ሁሉ ሲከናውን ደመነብሳዊ በሆነ ሂድት ውስጥ ነው: በእንግሊዝኛው Fight Flight and Freez የሚሉት ማለት ነው::

2. **Limbic/emotional/mammalian brian**

ይህን የአዕሮ ክፍል ደግሞ ከውሻ ከአይጥ ዶልፊን እና ከጦጣ ጋር እንጋራዋለን:: በዚህ የአንጎል ክፍል አማካኝነት ስሜታችንን የምንቆጣጠርበት ክፍል ሲሆን እንደየሁናቴው የሚቀያየር ይሆላል:: በዚህ ሊምቢክ በሚባለው የአንጎላችን ክፍል አሚዳላ/Amygdala የሚባል stress center አለ:፡ይህ stress center አደጋ መጣ ብሎ ሲያስብ መልዕክት ለ Reptials brian ይልካል ከዛ ረፐታይልስ ብሬን ለአደገ ዝግጁ ይሆንና ለመጣው አደጋ ሰዉየው ወይንም እንሰሳውን ዝግጁ እንዲሆን ያደርገዋል:: ደስታም ሆነ ሃዘን ፈቅርም ሆነ ጥላቻ በዚህ የአንጎል ክፈል አመካኝነት ነው የሚከናዎነው። ይህ የአንጎላችን ክፍል አዝጋሚ ለውጡን ተከትሎ ከረፐታይልስ አንጎል ቀጥሎ የመጣው የአንጎላችን ክፍል ነው።

3. **Frontallap/Logical/ rational bian የማሰቢያው ማሺን**

ይህ የአንጎል ክፍል ደግሞ በመጨረሻ የመጣውና ዘመናዊው የአንጎል ክፍላችን ነው:: ዘመናዊው ምክንያታዊው ሰው ይህን የአንጎል ክፍል በመጠቀም በሂዎት ያዳበረዉን ልምድና ዘወትር የሚመለከተውን ነገር ወደ ዉስጡ በማስገባትና process በማድርግ በዚህ የአንጎል ክፍል በመጠቀም እራሱን ከአካባቢዉ ጋር በማጣጣም በእውቅት የሚሰራበት ክፍል ነው:: በዚህ የአእምሮ ክፍል የሰው ልጂ ያየውን ነገር የሚያስታዉሰበት: እቅድ የሚያዎጣበት: ያሰበውን የሚያሳከበታ :ቋንቋን የሚጠቀምበት በዚህኛው የአንጎላችን ክፍል አማካኝነት ነው:: ከላይ የጠቀስኳቸው ሶስቱ የአንጎል ክፍላችንን PTSD ለተባለዉም ሆነ ለሌሎች ተዛማች የሆኑ የሰነልቦና ችግሮች ሲፈጠሩ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱ aktivate ሲሆኑ logical brian ከአገልግሎት ውጭ ይሆናል ምክንያቱም አደጋ ሲከሰት፡የሰው፡ልጂ፡Stress hormon፡ከፍ፡ሰለሚል፡በዚህ፡ግዜ እንስሳዊው የአንጎል ክፍላችን ብቻ፡እንዲሰራ፡ይገደዳል።

**ከዚህ በታች ደግሞ ሶስቱን የአንጎሎቻችን አቀማመጥ ከዚ በታች በስእላዊ መለክ ለማሳየት እሞክራለሁ።**




**PTSD[7] (POST TRAUMA STRES DISORDER) ማለት ምን ማለት ነው?**

:::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::: ::::::::::::::::::::::::::::::::::

እንደ ICD-10 disease clarification ምደባ መሰረት PTSD F43.1 በሚለው ክፍል ውስጥ ተመድቦ ይገኛል:: PTSD የሰው ልጅ በሂወቱ ያልጠበቀው መጥፎ ድብ እዳ ሁኔታ ውስጥ ሲገባ የሚከሰት የአእምሮ ችግር ነው:: መጥፎ ዱብ እዳ የሚባለው በሰው ልጅ አእምሮ ጠባሳውን ጥሎ ሲያልፍ ያ ጠባሳ ደግሞ በቀጠያይነት መጥፎ ነገሩ ካለፈም በሁላ እየተመላለሰ ልክ ሁኔታው አሁንም እየተከተለ እንደሚፈፀም አእምሮችን ሲነግረን ያለፍንበት መጥፎ ሁኔታ አሁንም እየተመላለስ እለታዊ ሂወታችንን ሲረብሺ እና ምንም ነገር ማድረግ ሲሳነን PTSD በሚባል በሺታ ተያዝን ማለት ነው:: ለPTSD ችግር ግብዓት የሚሆኑ ችግሮች ተፈጥሮዊ ወይንም ስውሰራሺ ሲሆኑ በእኛ አገር ገኖ የሚታየው ሰው ስራሹ ሰለሆነ ትኩረቴን እዛ አደርጋለሁ::አንድ ስው በእስር ቤት ውስጥ በጭካኔ መደብደብ ሲያጋጥመው፥በከባድ ጦርነት ውስጥ ሲታለፍ፥ ልጆች በህፃንነት ግዜቸው በወላጆቻቸው ሆነ በህ/ሰቡ ተገቢውን ፍቅርና እንክብካቤ ሳያገኙ ሲያድጉ (under or over stimulate) ሆነው ሲያድጉ ወይንም ደግሞሞ አሁን ቄሮ በተባለው ፅንፈኛ ቡድን እየተደረገ ያለው ዘግናኝ ግድያ በህፃናትም ሆነ በወጣቶች እንዲሁም በአዋቂዎች ሰነልቦና ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያልፍል::
ታዲያ ይህ ዘግናኝ ችግር ሁሌ እየተመላሰ ፋታ ሲነሳ ሁሌ በጭንቀትና በውጥረት ውስጥ ሆኖ ትናንት ያለፈውን መጥፎ ሁኔታ ዛሬም ይኖረዋል ማለት ነው:: በተለይ ህፃናት ችግሩ ወይንም ምልክቱ በታየ ማግስት ተገቢውን ክትትል እና ህክምና ካላገኙ ትምህርታቸውንም: ሰራቸውን በተገቢው መንገድ ማከናወን ይሳናቸዋል:: ምክንያቱም አእምሮቸው ሁሌ ያ መጥፎ ነገር አሁንም ሊከሰት ነው በሚል ዝግጁት (በmode of emergecy preparedness) ላይ ሰለሚሆን:: በዚግ ግዜ Reptials የተባለው የአንጎል ከፍላችን ነው activate የሚሆነው ማከንያቱም ጥንታዊው አንጎላችን የጥንቱን ደመነባሳዊ እንሰሳዊውን ሂዎት ሰለሚያስታውስ ያ ሊመጣ ነው ብሎ ሰለሚያሰብ እንዴት ከመጣበት አደጋ እንደሚታደግ ነው አእምሮው የሚያስበው:: በዚህ ግዜ አእምሮው በፈርሃትና በጭንቀት ሰለሚረድ በምክንያት የሚያሰብበት አእምሮ ይዘጋና ለተለያዩ የሰነለቦና ችግሮች የጋለጣል:: ለምሳሌ ለPTSD ችግር ሊጋለጥ ይችላል:: PTSD ችግሩ በተፈጠረ ማግስት ላይከስት ይችላል:: ብዙውን ግዜ ችግሩ ከተፈጠረ ከሁለት እሰከ ስድስት ወር ባለው ግዜ ውስጥ የPTSD ምልክቶች የሚከሰተቱት::

[7] https://www.sundhed.dk/borger/patienthaandbogen/psyke/sygdomme/oevrige-sygdomme/posttraumatisk-stressforstyrrelse/

## የPTSD[8] ምልክቶችስ ምን ምን ናቸው?

:::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::

1. ያለፈውን ዘግናኝ ሁኔታ እንደገና እየተመላለሰ ልክ አሁን እንደሚፈጠር ማሰብ (Flashbacks) እና ያሳለፍከውን ሁኔታ ዘወትር ማለም::
2. ካለፈው ዘግናኝ ሁኔታ ጋር ተዛማጂነት ያለው ነገር ስታይ በውስጥህ መጥፎ የሆነ ስሜት ሲሰማህና ፍራትፍራት ሲል:: ለምሳሌ በእስርቤት ውስጥ ድብደባ እና እንግልት ካየህ እና አሁን በሌላ ሁኔታ፥ቦታ እና ግዜ ላይ ሆነህ ፓሊስ ስታይ ፓሊሱን ካለፈ ሁኔታ ጋር በማያያዝ መፍራት::
3. የማስተዋል እና ትኩረት የማድረግ አቅም ሲጠፋ:
4. ከፍተኛ የሆነ ጭንቀት (stres) ውስጥ መኖር::
5. እና ስሜታዊ መሆን የሚሉት ከብዙ በጥቂቱ የሚታዩ ምልክቶች ናቸው::

## PTSD በአእምሮችን እንዴት ይከሰታል?

::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::::

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የሰው ልጂ በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፍና ያለፈው መጥፎ ሁኔታ አሁን እየመጣ ሲያስቸግረው የሰውየው አእምሮ ከጥንታዊዉ የአእምሮ ክፍል ጋር ( Reptials Brian) ነው ግንኙነት የሚያደርገው:: ምክንያቱም ህልውናው አደጋ ላይ ነው ብሎ ሲያስብ ልክ እንደ ጥንቱ በጫካው ህግ ዘመን እራሱን ከአደጋ ለመከላከል ወይ በድፍረት ፊት ለፊት ከጠላት ጋር መግጠም ነው: ወይ ነብሴን አውጭኝ ብሎ መሮጥ አለበለዚያ ደግሞ በፍርሀት እርዶ ባለበት ፈዞ መቅረትን ነው የሚያስበው:: በዚህ ግዜ የዘመናዊው ሰው rationalt/logically የሚያስብበት Frontallap የሚባለው የአንጎል ክፍል ሙሉ ለሙሉ ይዘጋል:: በዚህ ግዜ ከምክንያታዊ ትንታኔዎች ይልቅ የህልውናው ጥያቄ ይቀድምና ሰው በስጋት ፥ በፍርሀት እና በጭንቀት ውስጥ ተይዞ ይዳከራል:: ታዲያ በቁሮ በተፈፀመው ጭፍጨፋ ሰለባ የሆኑት ህፃናት ሁሌ ያዩት ነገር እየመጣ እንዳይረብሻቸውና PTSD ለተባለው የአእምሮ ችግር እንዳይጋለጡ በስነ ልቦና ህክምና ዘርፍ ያላችሁ ወገኖች በተሎ ወደ እርዳታው ሰራ ካልገባችሁ ነገ በእነዚህ ህፃናት ላይ ሊከሰት የሚችለው የስነ ልቦና ችግር በጣም የከፋ ነው የሚሆነው::
የሰው ልጂ ህልውናው አደጋ ላይ ነው በሎ ሲገመት ለምሳሌ የኮሮና በሺታ መጀመሪያ በመጣ ግዜ ሰው የተባለው ፈጡር ሁሉ አደጋ መጣ ብሎ ሰላላሰበ ዘዎትር ከሚያሳየው ባህሪ በወጣ መልኩ በሰግብግበነት ሁሉንም ነገር ለመገዛት እረጂም ሰልፍ ተሰልፎ የመጣበትን አደጋ ለመታደግ ሲሮጥ አይተናል ይህ ደግሞ እራሰን ከአደጋ ለመከላከልና የመጣውን አደጋ ለመሻገር Reptials berianን ተጠቅመናል።

ከዚህ በተጨማሪ ለመገልጽ የምፈልገው ነገር ቢኖር ደግሞ ስሞኑን ይፋ በኖነው የአለም አቀፍ IQ ተመራማሪ ድርጂት በአወጣው ዝርዝር ሪፖርት ኢትዩጲያ በጥናቱ ከተካተቱት 180 ሀገራት ውስጥ 163ኛ በመሆን በአለም የIQ ችግር ከካለባቸው ሀገራት ውስጥ የመጨረሻ ደረጃ ይዛለች:: የኢትዮጲያውያን IQ capacity 69[9] ደረጃ እንደሆነ ተገልጹል። ይህ ደገሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ አስተሳሰብ እንዳለን ያሳያል ይህ ማለት ምን ማለት ነው ሰንል ደገሞ የኢትዮጲያውያን መረጃን ወደ ጭንቅላታችን አሰገብተን ፕሮሰስ የምናደርገበት አቀም (cognition) መዳከምን፥ የተኩረት ማነስ ችግርን ፥የማሰተዋል እና የማሰታዎስ ችግር ሰለባ እንደሆን ያሳየናል። እነዚህ የጠቀስኩቸውን ነገሮች በመጠቀም ነው አእምሮችን በFrontalap አማካኘነት ምክንያታዊ እና ሎጂካል ሰራዎችን መተገበር የሚችለው። በአለም ትልቁ የIQ መጠን 140 ሲሆን አማካዩ ደገሞ 90 እስከ 110 ነው። ታዲያ ይህን ችግር ምን ፈጠረው ብንል ችግሩ ተፈጥሮዊም ሰዉ ሰራሺ እንደሚሆን ነው ጥናቶች የሚያመላከተቱት:: እኛ እንደ ማህበረሰብ መቀየር የምንችለውን ነገር ሰለሆነ አሁን አገራችንን ለመልከ በዙ ችግሮች ያጋለጣትን የነሳ ፖለቲካ ሰንቀየር እንደሃገር መፋቀረን መተሳሰበን ሰንሰብክ ሰው ሰራሺ የሆነውን የአሰተሳሰብ (IQ) ችግር ቀረፍን ማለት ነው። ጭንቅላታችን በጭንቀትና በሰጋት እና በፍርሃት ችግር ተተብትቦ አሰተሳሰበን ወደላቀ ደረጃ ማዉጣት የማየታሰብ ነው እና የአሰተሳሰብ ችሎታ ማነስ (lowes IQ) ቢያጋጠመን የሚገርም አይደለም ለማለት ነው።

---

[8] Ibid.

[99] Worldpopulationreview.com

ማጠቃለያ

ከላይ በተዎሰነ ደረጃ ችገሩን ለመገልጽ እንደሞከርኩት የችገሩ ሁሉ መንሰኤ አገሪቱ እየተመራች ያለችበት የጎሳ ፖለቲካ ሲሆን ይህም በአገሪቱ እየተፈጠሩ ላሉ ማናቸውም የህግ ጥሰቶች ለሰዎች መታረድ መገደል  መፈናቀል እና ለነገ ሃገር ተረካቢ በሆኑ ህፃናት ተሰፋ እና ጤንነት ጥቁር ጥላ ያጠላ ሰለሆነ ሁሉም ዜጋ ሊታገለው የሚገባ ችግር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጰያም ሆነ በውጭ ሃገራት የምተገኙ የሰነልቦናም ሆነ የስነአእምሮ ሃኪሞች በአገራችን እየተፈጠረ ባለው ዘግናኝ ጭፍጨፋ ምክንያት ለሰነልቦና ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናት እርድታ በተሎ ታደርጉላቸው ዘንድ አሳሰባለሁ:: አለበለሺያ ይህ ደግግሞሺ ቀጣይ ይሆንና (Vicious cycle) ወስጥ እንድንቀጠል ያደርገናል::

**ዋቢ መፃሃፍቶች**


1. ETNISKE MINORITETS FAMILIE OG SOCIALT ARBEJDE. HANS REITZELS FORALG 3.UDGAVE 1.OPLAG. (2007)
2. MODELLER I SOCIALT ARBEJDE HANS REITZELS FORLAG 2.UDGAVE 1.OPLAG. (2006)
3. PSYKOLOGI OG SOCIALT ARBEJDE AKADAMIK FORLAG 1.UGAVE 1.OPLAG (2017)
4. http://www.structuralviolence.org/structural-violence/
5. https://www.sundhed.dk/borger/patienthaandbogen/psyke/sygdomme/oevrige-sygdomme/posttraumatisk-stressforstyrrelse/
6. Worldpopulationreview.com